# ግልፅ ደብዳቤ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ

በቅድሚያ የከበረ ሰላምታዬን ከመልካም ምኞት ጋር እገልጻለሁ።

ዛሬ የምጽልፍዎ ደብዳቤ ሁለተኛዬ ነው፣ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ዘመን በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ስለቪዛ ጉዳይ ጽፌልዎ በእርስዎ ስም ቢሮዎ ወዲያው ከእውነት የራቀ መልስ ሰጡኝ፣ የእርስዎን ክብር ለመጠበቅ ብዬ መልሱ ከእርስዎ እንዳልመነጨ የሚገልጽ የመልስ መልስ ጻፍሁ፣ በዓመታት የሚቆጠር ጊዜ ቢፈጅም ያነሣኋቸው ጥያቄዎች ሁሉ ከሞላ ጎደል በትክክል ተመልሰዋል። ዛሬ የማነሣቸው ጥያቄዎች ግን የዓመታት ቀርቶ የቀናት ጊዜ የላቸውምና በጣም አጣዳፊዎች ናቸው፣ እርስዎ እንደተናገሩት የአገሪቱ ሁኔታ ወደ አደገኛነት የተጠጋበት ጊዜ ነው።

ማንም ሊክደው የማይችል አንድ እውነት አለ፣ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ፣ ፈልገው ይሁን ሳይፈልጉ መንገዱን ከሞላ ጎደል እያመቻቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመጨረሻ የነጻነት ጮራ እንዲያይና የሥልጣን ባለቤትነቱን እንዲገነዘብ ወደቻለበት አፋፍ ላይ አድርሰውታል። አሁን ወደ ቀጣዩ የሥልጣን መቆናጠጫው አፋፍ ላይ ሊያደርሱት ሲችሉና ሲገባዎም እንዴት፣ በጥላቻና በእልህ የገደል መግቢያውን መንገድ ቢያመለክቱት ቀድሞውንም አውቀውና ወደው ሳይሆን አንድ እቅድ ተጨናግፎብዎት እንደሆነ ተጨባጭ ማስረጃ ለታሪክ ባለሙያዎች ይሰጣሉ።

ዛሬ እርስዎና ቤተሰብዎ ብቻ ሳትሆኑ ለብዙ ዓመታት በየበረሀው የተንገላቱትን፣ የቆሰሉትንና የተሰውትን ጭፍራዎችዎንና ቤተሰቦቻቸውን በሙሉ፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሉ በተለያዩ መልኩ ከባድና ክፉ ፈተና ውስጥ እንደሚከቱት አይረዱትም ብዬ ለማመን ያስቸግረናል። አንድ ሰው ወይም የጥቂት ሰዎች ህልውና ከአገርና ከህዝብ ህልውና ጋር ሲመዘን ምን ያህል ቀላል እንደሚሆንም መስዋእት ከሆኑት ጓደኞቹዎ ሳይማሩ ይቀራሉ ብዬ አላምንም። ኢትዮጵያን ከትጥቅ ትግል አውጥቶ ወደ ፖለቲካ ትግል ውስጥ ማስገባት ለእኔ የታሪክ እመርታ ሆኖ ይታየናል። ይህንን ክብር ለራስዎና ለተወሰኑቱ ጓደኞችዎ ይነፍጋሉ ብዬ ለመገመት ያቅተኛል። ፍቅር፣ አመኔታና ተስፋ የሌለበት ፖለቲካ ምንም ዓይነት ፍሬ እንደማያፈራ የታወቀ ነው። አንዳንዴ ራስን በማሸነፍ የበለጠ ድልና ክብር ይገኛል።

እርስዎ እንደተቸገሩ በጣም ግልጽ ነው፣ ችግርዎ ለእኔ በደንብ ይገባኛል፣ በፕሬዝዳንትነትዎ ጊዜ አንዴ ተገናኝተን ኢ.ሕ.አ.ፓ.ና መድኅን በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ሳይሳተፉ መቅረታቸው ትክክል አለመሆኑን ስገልጽልዎት ለትጥቅ ትግል ስለተነሱ ከነሱ ጋር መነጋገር እንደማያስፈልግ በመደምደምዎ ሳንስማማ ተለያየን፣ ዛሬ ደግሞ በጣም ተለወጡና በሰላማዊ ትግል ምለው ለተነሱት ተቀናቃኝ ቡድኖች ፊትዎን ነስተው የቅድመ ሁኔታ ክምር እየደረደሩ ሲያስፈራሩ ኦነግን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለማነጋገር ፈቃደኛ መሆንዎ አንድ ችግር ያሳያል። እርስዎ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረጉበትን የሰላሙን ትግልና በዚያ ውስጥ የተሰለፉትን ሰዎች ንቀው በትጥቅ ከሚፎካከሩዎት ጋር ለመደራደር መሞከርዎ፣ በተለይ ኦነግን ሁለተኛ ጊዜ ላታልህ የሚል አዝማሚያ ማሳየትዎ ከማንኛውም ወገን ክብርን ለማግኘት አስበው ነው? በቅርብ ሆኖ ሰላም ሰላም እያለ የሚጮኸውን ሕዝብ

ነፍጠኛና ጦረኛ በማለት እያራቁና ተቀይሞ ወደ ትጥቅ ትግል የገባውን ሰላማዊ ማድረግ ሲሞክሩ ሁለቱንም ሞኞች አድርገው ነው? ወይስ አንዱን ብቻ? ዓለም አቀፉ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች መግለጫ በመንደርደሪያ ውስጥ የሚከተለውን ይላል

«ሰብዓዊ መብቶችን ችላ ማለትና መናቅ የሰውን ልጅ ኅሊና የአስጨነቁ አረመኔአዊ ተግባሮችን በማስከተላቸውና የተራ ሰዎችም ሁሉ ዋነኛው ጉጉት የሰው ልጆች ሁሉ የንግግርና የእምነት ነጻነት የሚጎናፀፉበት፣ ከፍርሃትና ከችግር ነጻ የሚወጡበት ዓላማ እንዲመጣ ነው።…

ሰዎች በክፉ አገዛዝና በጭቆና የተነሣ ያላቸው የመጨረሻ ምርጫቸው ዓመፅ እንዲሆን እንዳይገደዱ ሰብአዊ መብቶች በሕግ እንዲከበሩ ማድረጉ አስፈላጊ ነው።

ኦነግ በመጋበዙ መቶ በመቶ እስማማለሁ። የእርስዎ ችግር ሆኖ የሚታየኝ ሰላማዊ የፖለቲካ ቡድኖችን ወደ ዳር እየገፉ የኦነግን ቦታ እንዲይዙልዎ መሞከርዎ ነው። ማንኛውም ተቀናቃኝ ቡድን ኦነግ ወደ ሰላማዊ ትግል እንዲገባ የሚፈልግ ይመስለኛል። በአንፃሩ ደግሞ ከርስዎ ሎሌዎች አንዱ የኦሮሚያን የመገንጠል ጥያቄ እናቀርባለን ሲል ምኞቱን ገልጿል ይባላል። ይህንን አደናጋሪ መልእክት ኦነግ ይስተዋል ተብሎ ነው?

ችግርዎ በሌላም አቅጣጫ እየታየ ነው፣ ትግራይን የማስገንጠል ጉዳይም ወሬ ሆኗል፣ ነገሩ አስቂኝ ቢሆንዎ ያሳዝናል፣ ወይ እኔ ስለትግራይ ሕዝብ የማውቀው ሁሉ ፈድሞ የተሳሳተ ነው፣ ወይ እርስዎ ስለትግራይ ሕዝብ ያለዎት ግንዛቤ ከግል ስሜትዎ የሚያልፍ አይደለም። ቀደም ሲል እንደተናገርኩት ፍቅር ካለበት ልብ ይህ ምኞት አይወጣም። ለመሆኑስ አሁን ትግራይ ያለበትን መከራና ስቃይ፣ እያንዣበበበት ያለው አደጋ የማያበቃው ሆኖ ነው ወይ ሌላ ችግር የሚጠነሰስለት?

በሕይወቴ ለማየት የምፈልገው ሁለት ሕልም ነበረኝ አንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱ ባለቤት፣ የአገሩ ባለቤት ሆኖ ከፍርሃት ነጻ ሆኖ ሃሳቡንና ፈቃዱን በአደባባይ ሲገልጽ ማየት ነበር ይህንን ሚያዝያ ሠላሳና ግንቦት ሰባት አየሁ ለዚህ ከልቤ አመሰግንዎታለሁ። ሁለተኛው ሕልሜን እደርስበት እንደሆነ አላውቅም። ለአሥር ዓመታት በነጻነትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ከቆየች ኢትዮጵያ የአፍሪካ ጃፓን የመሆኑን ጉዞ ትጀምራለች የሚሉ ጽኑ እምነት አለኝ። እባክዎ ይህንን እርስዎ የጀመሩትን የዴሞክራሲ ጉዞ ወደ ደም መቃባት አይለውጡት በደም መቃባቱ ከሁሉም ወገን የሚጎዳው ገና የኑሮን ጣዕም ያልቀመሰውና በልቶ ያልጠገበው ወጣት ነው ይዘኑለት ይራሩለት።

አቶ መለስ፣ እባክዎ ልብዎን ለፍቅር፣ አእምሮዎን ለታሪክ ይክፈቱና ይህ የተሰቃየ ሕዝብ በዴሞክራሲ ጎዳና ከስሕተቱ እየተማረ እንዲገሰግስና ከድህነትና ከችጋር እንዲወጣ የከፈቱትን በር አይዝጉበት በልጆችዎ፣ በተሰውት ጓደኞችዎና በኢትዮጵያውያን እናቶችና አባቶች ስም እማጸንዎታለሁ።

**ትሑት ታዛዥዎ**
መስከረም 18/ 1998 ዓ.ም
**መስፍን ወልደ ማርያም።**

ከዘ ሞኒተር መስከረም 20 ቀን 1998

ሰለ እዚህ ዜና ዋርካ ስር በአማርኛ ይወያዩ !